# ቀላጤ አርቃቂው ጠ/ምኒስትር

ታሪኩ አባዳማ ጥቅምት 2003

በዚች ገጠር ወረዳ ብቸኛ ቀላጤ ፀሀፊ የሆነው 'አስናቀ ሽቦ' ሰዎች ሲካሰሱ ፣ አቤቱታ ሲያቀርቡ ፣ ውል ሲፈራረሙ ረቂቅ አዘጋጅቶ በገፅ አንድ ብር እያስከፈለ ቀላጤ ይቸከችካል።

ታዲያ ከዕለታት አንድ ቀን በዚያች ገጠር ከተማ ሁከት ይቀሰቀሳል። በርካታ ህዝብ ባንድነት ተሰብስቦ እየዘመረ ፣ እያወገዘ ወደ ዘመቻ ጣቢያው ይተማል። የዚህ አይነቱ ህዝባዊ ሁከት ከአብዮቱ ወዲህ እተለመደ የመጣ በመሆኑ ብዙ የሚያስገርም አልነበረም። ገበሬዎች በሆታ ተሰልፈው አድሀሪ ፣ በዝባዥ የሚሉትን ሰው አጅበው እየዘመሩ ለዘማቾች ሲያስረክቡ ብዙ ግዜ ታይቷል። የዚያን ዕለቱ ሁካታ ለየት የሚለው ግን ከሚጓዘው ህዝብ ፊት እየተጣደፈ አልፎ አልፎ ወደ'ሚያሳድደው ሰልፈኛ ገልመጥ እያለ ወደ ዘመቻ ጣቢያው የሚገሰግሰው 'አስናቀ ሽቦ' መሆኑ ነው።

ምናለ ህዝቡ ምናለ<br>አስናቀ ሽቦ ፣ አስናቀ ሽቦ ካገር ይውጣ አለ

ምስኪኑ አስናቀ እንደ ወትሮው ኩታውን አጣፍቶ እንደለበሰ ወደ ዘመቻ ጣቢያው በሽሽት እየገሰገሰ ነው - ህዝቡ ከሁዋላው እየዘመረ ይከተለዋል። በዛፍ ቅጠል እራሱን ያጀበው ሰልፈኛ ከዘመቻ ጣቢያ ግቢ ሲደርስ በጋለ ቁጣ እና በጩኸት መዘመሩን ቀጠለ። አስናቀ ሽቦ በበኩሉ ከቅጥር ግቢ ወደ ውስጥ ገባ ብሎ ካንድ ጥግ እጁን እያወናጨፈ የሆነ ነገር ለዘማቾቹ ይነግራል። በመጨረሻ የዘመቻ ጣቢያው ሀላፊ መቶ አለቃ ህዝቡን አረጋግተው እና በሜዳው ላይ አስቀምጠው ሲያበቁ 'ምንድነው ችግሩ' ብለው ሰልፈኛውን ይጠይቃሉ።

"ይህ ሰው" አሉ አንድ አዛውንት ሰልፈኛ ተነስተው "… አንድ ጭቁን ከሌላ ጭቁን ጋር እያጋጨ ሰላም ስለነሳን አካባቢያችንን ለቆ እንዲሄድልን ነው የምንፈልገው… ደግሞ ከአድሀርያን ጋር ነገር ያቀባብላል…" በደም ፍላት ክሳቸውን አሰሙ። ነገሩ የሆነው ከዛሬ ሰላሳ አመታት በፊት ነበር።

መቶ አለቃ ማብራሪያ ይጠይቃሉ "እሱም እኮ እንደናንተው ጭቁን ነው … እንዴት ነው የሚያጋጫችሁ… ደግሞስ መኖሪያውን ለቆ የት ይሂድ"? መቶ አለቃ ንትርኩን በአብዮታዊ መነፅር ለማመዛዘን እየሞከሩ ይመስላል።

"ለከሳሽ እና ለተከሳሽ ለሁለቱም ወገን ቀላጤ የሚፅፈው እሱ ነው … ለጭቁን እና ለአድሀሪ ሳይለይ ቀላጤ የሚያረቀው እሱ … ሰው ያልተናገረውን እየፈጠረ ፣ የሌለውን እየጨማመረ … ያንዱን ደካማ ጎን ለሌላው እየሸጠ እያነካካ ፣ ነገር እያከረረ ችግራችን ተባብሶ በሰለም እና በእርቅ እንኳን እንዳንገላገል እርስ በርስ ደመኛ አድርጎ ሰላም ነስቶናል… እሱ ከዚህ አካባቢ ካልጠፋ ህዝቡ በሰላም መኖር አይችልም… እዚህ ቆያለሁ ካለ ለሚደርስበት አደጋ ህዝቡ ሀላፊ አይሆንም… የህዝቡን ብሶት ሰምታችሁ መፍትሄ እንድትሰጡ እንጠይቃለን…" ሰልፈኛው በየተራ እየተነሳ ቁጣውን ገለፀ።

አስናቀ ሽቦ ድሮም በካቲካላ የደቀቀ አመዳም ፊቱን አኮማትሮ "በህግ አምላክ ብያለሁ … በደርጉ ብያለሁ… አገሬን ጥዬ የትም አልሄድም … ሰርቼ መብላት የሚከለክለኝ የለም … አስገድኜ ያስፈረምኩት ሰው የለም … ደምበኞቼን ደስ ማሰኘት ደግሞ ሥራዬ ነው… በህጉ መሠረት። ምን አድርግ ትሉኛላችሁ…" እያለ የበኩሉን ተናዘዘ። አስናቀ መሬት የለው በሬ የለው ፣ ጭቁን አድሀሪ በሱ ዘንድ ትርጉም ያለው ነገር አይደለም። የመጣውን ማስተናገድ ፣ ብሶት አዳምጦ ቀላጤ ማርቀቅ ነው ሥራው። በደምብ ለከፈለው አሳምሮ ይጽፋል ፣ ክፍያው ላይ ጨምሮ ካቲካላ ለጋበዘው ደግሞ እዚያው ካቲካላ ቤት ያረቀቀውን እንደ እሳት የሚፋጅ ቀላጤ ለደንበኛው ያቀርባል።

መኪና የሚያስገባ መንገድ እንኳ ባልነበራት በዚያች የገጠር ወረዳ ማንበብ እና መፃፍ የሚችል አቅመ አዳም የደረሰ ሰው ፈልጎ ማግኘት ለነዋሪው ከባድ ነበር። መፃፍ ቢችል እንኳ ነገር አስማምቶ ፣ የህግ አንቀፅ ጠቅሶ ቀላጤ የሚያዘጋጅ ሰው ገንዘብ ተከፍሎም ቢሆን ማግኘት ይቸግራል። በወረዳው የነበረው ብቸኛ ቀላጤ ፀሀፊ አቶ አስናቀ ነው - በአካባቢው ነዋሪ 'አስናቀ ሽቦ' በሚል ቅፅል ይጠራል። አስናቀ ሽቦ እንደ አቶ መለስ ቁመቱ አጭር እና ጉጭማ ሲሆን አረማመዱ አንካሳ ሰለሚመስል 'ሽቦ' (ሽባው እንደማለት) ብለው ያሽሟጥጡታል።

ቀላጤ ፀሀፊ ብዙ ችግር ያጋጥመዋል። ወደፊት ላቀርበው በማስበው እውነተኛ ታሪክ ውስጥ ከሚካተቱ ጉዳዮች ቀንጨብ አድርጌ እንደ መግቢያ ያቀረብኩት ግን አለምክንያት አይደለም።

በሰለጠነው አለም ሳይቀር የህግ አዋቂዎች ለደምበኞቻቸው ቀላጤ በማርቀቅ ሁነኛ ገንዘብ እየተከፈላቸው ይሰራሉ። ከዚያም አልፎ የፖለቲካ መሪዎች በአደባባይ ይሁን በዝግ የፓርቲ ስብሰባ ላይ የሚያደርጉትን ንግግር የሚያዘጋጁ በከፍተኛ ደሞዝ ተቀጥረው የሚሰሩ ራፖር ፀሀፊዎች /speech writer/ አሏቸው።

ፀሀፊዎቹ መደበኛ ሥራቸው መሪው በተወሰነ ጉዳይ ላይ ያለውን አቋም የሚያንፀባርቅ ፅሁፍ ማርቀቃቸውን ማረጋገጥ ነው። የመሪውን አቋም በተለያየ ግዜ እራሱ ከሰጣቸው አስተያየቶች ያጠናቅራሉ ፤ ይህንንም ከፓርቲው ፖሊሲ እና ካገሪቱ ህገ መንግስት አኳያ አስማምተው ይቸከችኩታል። መሪ ብዙ ሀላፊነት ስላለበት የራሱን ንግግር እንኳን ለማዘጋጀት ግዜው የለውም። ይሄ ደግሞ በፈረንጆቹ አለም ነው።

በዘመነ ወያኔ እኛ አገር ነገሩ የተገላቢጦሽ ሆኗል። መሪ ነኝ የሚለው ሰውየ ለእስረኛ ሳይቀር የምህረት መጠየቂያ ቀላጤ እያረቀቀ ነው። “ፈረንጅ ያስፈታኛል ብላ…” እያለ በየመድረኩ ሲመፃደቅበት የነበረውን ፈሊጥ ወደ ሰነድነት ተርጉሞ የወንጀል አስረጂ አድርጎ አቅርቦታል።

በአንድ ገፅ የተካተተው የወ/ት ብርቱካን ‘የምህረት መጠየቂያ’ ቀላጤ ከታሰረችበት ዕለት ጀምሮ አቶ መለስ በየመድረኩ ስለሷ ሲናገር የነበረውን ዝባዝንኬ እጥር ምጥን አድርጎ ያካተተ ወረቀት ከመሆኑ አንፃር ሰውየው ጥሩ አስናቀ ሽቦ ሊወጣው እንደሚችል አሳይቶኛል። በመለስ ተነግሮ የተረቀቀ በብርቱካን የተፈረመ ሰነድ ቢባል ነገሩን ያሳምረዋል።

አስናቀ ሽቦ ቀላጤ ያረቅ የነበረው በደምበኝነት ለከፈሉት ሰዎች ብቻ ሲሆን መለስ ዜናዊ በራሱ ቀጭን ትዕዛዝ ላገታቸው ዜጎች ሳይቀር ቀላጤ የሚያረቅ መሆኑ የተለያየ ባህሪ እንዳላቸው ያመለክት ይሆናል። በዚህ ረገድ አስናቀ ሽቦ ሰብአዊነት ያልተለየው ፣ ሥራውን አክብሮ በትጋት ያከናውን የነበረ ሰው ነበር ማለት ይቻላል።

አምባገነንነት አይነተኛ መለያ ባህሪው ለሰብአዊ መብት አንዳችም ክብር የሌለው መሆኑ ነው። ሰብአዊ መብትን መርገጥ ፣ ሌሎችን ማብጠልጠል እና ማዋረድ ለሚመኘው  ስልጣንና የበላይነት መረጋገጥ መሠረት ነው ብሎ ያምናል። ፀሀይ የሞቀው ውሸት ለመዋሸት የሚከለክለው ህሊና የለውም። ይህን ወራዳ ድርጊት ለመፈፀም ደግሞ የተቀመጠበት ወንበር እና ለራሱ የሰጠው ማዕረግ አያግደውም። ጠቅላይ ምኒስትር መለስ ዜናዊ በገዛ ራሱ ቀጥተኛ ትዕዛዝ እንበለ ሕግ ወህኒ የወረወራትን ንፁህ ዜጋ እራሱ ባረቀቀው ቀላጤ ምህረት ጠይቂኝ ብሎ መፍታት ሰውየው ምን ያህል ተራ እና ተርታ ስብዕና ያለው መሆኑን ለሁሉም ይበልጥ አረጋግጧል።

ባለፈው ሰሞን ኮለምቢያ ዩንቨርሲቲ አንድ የስብሰባ ተሳታፊ በመንግሥቱ ሀ/ማርያም እና በሱ አስተዳደር መካከል ምንም ልዩነት እንደሌለ ሲነግረው ምን ብሎ እንደመለሰ ብዙዎቻችሁ ያጤናችሁ አይመስለኝም።

መለስ በወቅቱ እንደተናገረው “በመንግስቱ ዘመን ዜጎች ለሚገደሉበት ጥይት ገንዘብ ይከፍላሉ … ያ አሠራር በኔ አገዛዝ ቦታ የለውም ፣ ተደምሰሷል” ብሎ መቀጠል አልቻለም (ቪዲዮውን ፈልጋችሁ እዩት)።

እንደሱ አባባል ‘በኔ አስተዳደር ዜጎች ስንገድል የጥይት ዋጋ አንጠይቅም…’ ማለቱ ነው። እየገደለ ፣ እያሰረ ፣ ህዝብ እያሸማቀቀ  ስልጣን ላይ መቆየቱን አልካደም - ይሁንና የገደለበትን ጥይት ዋጋ ስለማይጠይቅ ከመንግስቱ እሻላለሁ ብሏል። እንደ አስናቀ ሽቦ ለደምበኞቹ ገንዘብ ተቀብሎ ሳይሆን በፖለቲካ ደመኝነት ላሠራቸው ዜጎች በነፃ ቀላጤ የሚያረቅ ጠ/ምኒስትር ስለሆነም የተሻለ ማመልከቻ ፀሀፊ መሆኑን ብቻ ሳይሆን በአለም ላይ ብቸኛ ቀላጤ አርቃቂ መሪ መሆኑን ጭምር አስመስክሯል። ብራቮ ክቡር ቀላጤ አርቃቂ።